ሐምሌ 28 ቀን 2006 ዓ.ም
የኮ.መ.ቁ 155040

ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት
19ኛ ወንጀል ችሎት
አዲስ አበባ

ከሣሽ፡- ..................የፌደራል ዐቃቤ ሕግ

ተከሣሾች፡- .............እነ ሶልያና ሽመልስ ገ/ማርያም(10 ሰዎች)

በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 112፣130 እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 73514 ( ቅጽ 14) በሰጠው የሕግ ትርጉም መሠረት ከ2-8 እና 10ኛ ተከሣሾች የቀረበ የክስ መቃወሚያ፡-

ከሣሽ በ08/11/06 ዓ.ም ፣በቁጥር በፌ/ማ/ዓ/ሕ/05/07 በተሻሻለ በተከሣሾች ላይ ሁለት ክሶችን አቅርቧል፡፡ ክሶቹም፡- 1ኛ ክስ- ተከሣሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ እና ለ፣ 38(1) እና (2)፣ እንዲሁም የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4 ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ የሽብርተኝነት ወንጀል ለመፈፀም አቅደዋል፣ተዘጋጅተዋል፣ አሲረዋል እንዲሁም አነሣስተዋል የሚል ሲሆን፣ 2ኛው ክስ - ደግሞ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 27/1/ሀ/ለ፣ 32/1/ሀ እና ለ፣ 38(1) እና አንቀጽ 238/1/ሀ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በሁከትና በአመጽ ለመለወጥ በማሰባቸው በዋና ወንጀል አድራጊነት በፈጸሙት በሕገ መንግስትና በሕገ መንግስታዊ ሥርዓት ላይ በሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ በመሆኑም የተከሣሾች መቃወሚያ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በ1ኛ ክስ ላይ የቀረበቡ መቃወሚያዎች

በቀረበው ክስ ተፈፀመ የተባለው ድርጊት ከተጠቀሰው የሕግ አነጋገር ጋር የተቀራረበ ስላለመሆኑ ( የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር112)

በመጀመሪያው ክስ ተከሣሾች ተላልፈዋል በሚል የተጠቀሰባቸው የሕግ አንቀጽ የፀረ- ሽብርተኝነት አዋጁ አንቀጽ 4 ነው፡፡ በዚህ የአዋጁ አንቀጽ 4 ድንጋጌ መሠረት ለክስ የሚያበቃውና በማስረጃም ቢረጋገጥ ሊያስቀጣ የሚችለው በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 3 ላይ "የሽብርተኝነት ድርጊቶች" ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዱን ወይንም ሁለቱን ወይም ከዚያ በላይ የሆነውን ድርጊት(ቶች)ለመፈጸም ያቀደ፣ የተዘጋጀ፣ ያሴረ፣ያነሣሣ ወይም የሞከረ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው 1ኛው ክስ "...ተከሣሾች በሕቡዕ ተደራጅተዋል፣ አቅድ አውጥተዋል፣ ሥልጠና ወስደዋል እና ገንዘብ ተቀብለዋል... "ከሚል በቀር በአዋጁ አንቀጽ 3 ሥር "የሽብርተኝነት ተግባራት " ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ የትኛውን " የሽብርተኝነት ተግባር" ለመፈጸም እንዳቀዱ ፣እንደተዘጋጁ፣ እንዳሴሩ ወይም እንዳነሣሱ አልገለጸም ፡፡ በዚህ ሁኔታ የቀረበው ክስ ወ/መ/ሥ/ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 112 "...ስለወንጀሉና ስለ ሁኔታው የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ወንጀለኛው የፈጸመው ተግባር ወንጀል የሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን አለበት..." በማለት በአስገዳጅነት የደነገገውን የክስ አቀራረብ መርህ የተከተለ አይደለም ፡፡ ስለሆነም ተከሳሾች በጸረ ሽብርተኝነት አዋጁ አንቀጽ 3 ከተዘረዘሩት "የሽብርተኝነት ተግባራት መካከል አንዱንም ለመፈጸም አቀዱ- አሴሩ ባልተባለበት ሁኔታ በአቃቤ ሕግ ተዘጋጅቶ የቀረበው ክስ ከአስገዳጅ ከሆነው የሥነሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ ውጪ የቀረበ ብቻ ሳይሆን ተከሣሾች ፈጽመውታል ተብሎ በክሱ ዝርዝር የተገለፁት ድርጊቶች "የሽብርተኝነት ተግባራት" ስላለመሆናቸው በግልጽ የሚታይ በመሆኑ የተከበረው ፍ/ቤት ከሕግ ውጪ የቀረበውን ክስ ሰርዞ ተከሣሾችን በነፃ እንዲያሰናብተን እናመለከታለን፡፡

ተከሣሾች ፈፅመዋቸዋል ተብሎ በክሱ ዝርዝር የተመለከቱት ተግባራት በሕግ የተፈቀዱና ሕገ-መንግስታዊ ጥበቃም የተደረገባቸው ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ስለመሆናቸው እና የወንጀል ኃላፊነትን የማያስከትሉ ስለመሆናቸው(የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 2) ፣ (የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ-መንግስት አንቀጽ 26፣29 እና 31)

በኢ.ፌ.ዲ.ራ.ሕገ-መንግስት የግል ሕይወት የመከበር እና የመጠበቅ መብት (Right to privacy)(አንቀጽ 26)፣ ሐሣብን በነፃ የመግለፅ እና የመረጃ ነፃነት ( አንቀጽ 29)፣ እንዲሁም የመደራጀት መብት (አንቀጽ 31) በግልጽ ተከብረዋል፡፡ እነዚህ በሕገ- መንግስቱ ዕውቅና ተሰጥቷቸው ጥበቃ የተደረገላቸው ሰብዐዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን "...... ሕግ አውጪው፣ አስፈፃሚው እና የዳኝነት አካሎች

የማክበር እና የማስከበር ኋላፊነት እና ግዴታ አለባቸው....."(<u>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት</u> አንቀጽ13)፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ሕዳር 6 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 73514( ቅጽ 14) በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ፍ/ቤቶች በዐቃቤ ሕግ የቀረበ የወንጀል ክስ በሕገ-መንግስቱ እና በወንጀል ሕጉ የሰብዐዊ መብቶችን ለማስከበር የተቀመጡ መርሆችን እና ድንጋጌዎችን የሚያሟሉ መሆን አለመሆኑን በመመርመር የመወሰን ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ አስቀምጧል፡፡

ይሁን እንጂ በከሣሽ ዐቃቤ ሕግ በቀረበው ክስ የተከሣሾች የመደራጀት፣ መረጃ የማግኘትንና የመስጠት እንዲሁም ሃሳብን በነፃ የመግለጽ እና የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ ሕገ-መንግስታዊ መብትን በግልጽ በሚቃረን ሁኔታ መደረጃታቸውን ፣ መረጃ መስጠታቸውን፣ መፃፋቸውን እና ከመንግስት የፀጥታ ኃይሎች እና ከመገናኛ አውታሮች ውጪ መልዕክት ለማስተላለፍ የሚያስችላቸው ነው ተብሎ በክሱ ዝርዝር የተገለጸውን (Security in box ) ስልጠና ወስደዋል በማለትና ወንጀል አስመስሎ በማቅረብ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 13 ላይ የተጣለበትን ግዴታና ሐላፊነት የሚጥስ ተግባር ፈጽሟል፡፡ በመሆኑም የተከበረው ፍ/ቤት ከላይ በጠቀስናቸው የሕገ-መንግስቱ ድንጋጌዎችና እና የሰበር ሰሚ ችሎቱ ውሣኔ መሠረት ባለበት ኃላፊነት የቀረበው ክስ የተከሣሾችን ሰብዓዊና ዲሞክራሲ መብቶች ያላገናዘበ እና የሚጥስ ነው በማለት ክሱን እንዲሰርዘው እናለመለከታለን፡፡

1.3. <u>የቀረበው ክስ ግልጽ ስላለመሆኑ እና ተከሣሾች የተከሰሱበትን ጉዳይ ለይተው አውቀውና ተረድተው ለመከላከል የማያስችል ስለመሆኑ፡-</u>

<u>(የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ/111)</u>

ከሣሽ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው 1ኛ ክስ ዝርዝር ውስጥ ፡-

- ክስ የቀረበበት ድርጊት ተፈጸመ የተባለበት ጊዜ በአጠቃላይ ከግንቦት 2004 ዓ.ም. ጀምሮ ከሚል በቀር ተከሳሾች ፈጽመውታል ተብሎ የተከሰሱበት እያንዳንዱ ድርጊት ተለይቶ መቼ እና የት ስልጠና እንደወሰዱ፣ ገንዘብ እንደተቀበሉ፣ እስትራቴጂ እንደቀረጹ ወዘተ.. በክሱ ዝርዝር አልተገለጸም፡፡
- "<u>ቡድን</u>" እና "<u>ድርጅት</u>" የሚሉትን ቃላት በተለዋዋጭነት የተጠቀመባቸው ከመሆኑም በላይ ቡድን ወይም ድርጅት እያለ የሚጠራው ተከሣሾችን ይሁን፣ እነሱ አዳራጁቸው የተባሉትን ይሁን ወይም ሌላ በግልጽ አላስቀመጠም፣
- "<u>በሕቡዕ</u>" የሚለው ቃል የሕግ ቋንቋ ( አነጋገር) ካለመሆኑም በላይ ከሣሽ የተጠቀመበት የትርጉም አግባብ ግልጽ አይደለም፡፡ተከሳሾች ሳይመዘገቡ ተደራጅተዋል ለማለት ተጠቅሞበት ከሆነም በግልጽ ይህንኑ ማለት ሲገባው አላለም፡፡
- ተከሣሾች መሠረቱት የተባለው ቡድን ወይም ድርጅት <u>ስም</u> አልተመለከተም፡፡ ክስ የቀረበባቸው ከፊል ተከሣሾች "<u>ዞን 9</u>" ተብለው ይታወቁበታል በሚባለው ስያሜያቸው ከሆነም የቀረበባቸውን ክስ በግልጽ ተረድተው መከላከል ይችሉ ዘንድ ይኼው በግልጽ ተመልክቶ መቀመጥ አለበት፡፡
- "<u>....የውስጥ የሥራ ክፍፍል ፈጥረው....</u>" በሚል በተከሣሾች ላይ የቀረበው ክስ ማን የቡድኑ ሊቀ-መንበር፣ ማን የውጭ ጉዳይ ክፍል፣ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል እና የዘመቻና የምርመር አስተባባሪ እንደሆኑ ተገልፆ አልቀረበም፣
- "<u>...ተልዕኮ በመቀበል...</u>"ተብሎ በተገለፀው አባባል ማን፣ምን ዓይነት ተልዕኮ፣መቼ እና ከማን እንደተቀበሉ አልተገለጸም፡፡
- በተመሣሣይ "<u>..የግንቦት ሰባትን መግለጫና የአነግን የፓለቲካ ፕሮግራም ለቡድኑ መመሪያ በማድረግ..</u>" ተብሎ በክሱ የተገለፀው አባባል በምን መንገድ መመሪያ እንዳደረጉት አይገልጽም፡፡
- "<u>..ግቡን ለማሣካት ስትራቴጂ ቀርፀው..</u>" የሚል አባባል የተቀመጠ ቢሆንም ግብና ስራቴጂ የተባለው ምን እንደሆነ በግልጽ አልተቀመጠም፡፡
- ተከሣሾች የተለያዩ"... <u>ሥልጠናዎች በመውሰድና በመስጠት..</u>" ክስ የቀረበባቸው ቢሆንም፣ ተሰጠም ሆነ ተወሰደ የተባለው ሥልጠና መቼ እንደተሰጠ፣የት እንደተሰጠ፣ ስልጠናውን ያዘጋጀውና የስልጠናው ባለቤት ማን እንደሆነ፣ ሥልጠናው በምን ርዕስ ላይ እንደተደረገ በግልጸ የማያመለከት እና የቀረበባቸው ክስ በየትኛው ሥልጠና መሆኑን ተረድተው ለመከላከል እንዲችሉ የማያደርግ ነው፡፡
- 3ኛ ተከሣሽ ተቀበለ የተባለው <u>ብር 48፣000.00(አርባ ስምንት ሺህ ብር)</u> ከማን እንደተቀበለውና ለምን ተግባር እንዳዋለው አልተገለጸም
- ተከሣሾች "<u>...ለኢሣት ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያ ሪፖርት ሲያደርገው ሕቡዕ ቡድኑ ድጋፍ እንዲያገኝ አድርገዋል...</u>" በሚል በቀረበባቸው ክ ሕቡዕ የተባለው ቡድን የትኛው ቡድን እንደሆነ እና ያገኘው ድጋፍ ምን እንደሆነ በግልጽ አልተመለከተም፣
- "<u>..የግንቦት ሰባት ሕቡዕ አመራር..</u>" በሚል በክሱ በተከተተው አባባል ሕቡዕ የተባለው አመራር የት እንደሚገኝ እና ማን የሚባል እንደሁ አያመለከትም፡፡

ከፍ ብሎ በዝርዝር የተመለከቱት ግልፀ ስህተቶችና ክፍተቶች በግልጽና በዝርዝር ተለይተው ባልተገለጹበት ሁኔታ በዐቃቤ ሕግ ተዘጋጅቶ የቀረበው ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 111 የተደነገገውን የክስ አቀራረብ ሥርዓት የማያሟላ፣ ተከሳሾች ስለተፈፀመው ክስ በግልጽ አውቀውና ተረድተው የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ የማያስችልና፣ ከስህተቶቹ(ጉድለቶቹ)መሰረታዊነትና በርካታነት አንጻር ስለክሱ ተረድቶ መከላከል ጭርሱኑ አዳጋች በመሆኑ፡ የተከበረው ፍ/ቤት የተረበውን ክስ ውድቅ እንዲያደርገው በማክበር እናመለከታለን፡፡

1.4. <u>ተከሳሾች ወስደዋቸዋል የተባሉት ሥልጠናዎች እና ለመገናኛ ብዙሃን መረጃ ማስተላለፍ ወንጀል ስላለመሆኑ፡</u>

ተከሳሾች.. መልዕክት በሚስጥር ማስተላለፍ የሚቻልበትን ዘዴ፣ አመጽ አመራር፣ የሕዝብ ቅስቀሳ ዘዴ፣ የተቀጣጣይ መሣሪያዎች አሠራር እና አጠቃቀም ሥልጠና ወስደዋል.. " የሚል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡ ሆኖም ከእነዚህ ተከሳሾች ወሰዷቸው ተብሎ በቀረበው ክስ ከተመለከቱት ሥልጠናዎች እንዳቸውም የወንጀል ተግባርን አያቋቁሙም፡፡ ከሳሽ ዐቃቤ ሕግም እነዚህ ሥልጠናዎች እንዴት ወንጀል እንደሆኑ በክሱ አላመለከተም፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ ኢሣት ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያ <u>"..የግንቦት ሰባት ልሣን.."</u> ነው ተብሎ በክሱ የተገለጸው አባባል እንደ ቅቡል ግምት ( *judicial notice* ) ሊወሰድ የማይገባ ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተቃራኒው ዐቃቤ ሕግ የቴሌቪዥን እና የሬዲዮ ጣቢያው የግንቦት ሰባት ልሣን እንደሆነ ግምት ለማሣደር በመሞከር ተከሣሾች ለዚህ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያ መረጃ አስተላልፈዋል በሚል የወንጀል ክስ ማቅረቡ በሕግ ወንጀል ነው ተብሎ ያልተከለከለን ድርጊት ወንጀል አድርጎ ማቅረብ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

1.5. <u>ዐቃቤ ሕግ ተከሣሾችን የሽብር ቡድን አባል አያለ ያቀረበው ክስ አዋጁን እና ሕገ-መንግስቱን የጣሰ ስለመሆኑ፡-</u>

ተከሣሾች ያደራጁት ቡድን <u>"..የሽብርተኛ ቡድን..."</u> ተብሎ በክሱ ላይ ተመልክቷል፡፡ አንድን ቡድን በጸረ-ሽብርተኝነት <u>አዋጅ አንቀጽ 25</u> መሠረት ሽብርተኛ ብሎ የመሠየም ሥልጣን የተሠጠው <u>ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት</u> ሆኖ እያለ፣ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ቡድኑን ሽብርተኛ ብሎ እንዳልሠየመው እየታወቀ በዐ/ሕግ ክስ ቡድኑ "<u>ሽብርተኛ</u>" ተከሣሾች ደግሞ "<u>የሽብር ቡድን አባል</u>" ተብለው መጠራታቸው የአዋጁን ድንጋጌ የጣሰ ብቻ ሳይሆን በሕገ መንግስቱ <u>አንቀጽ 20/3</u> ተከሣሾች ያላቸውን <u>እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት</u> በግልጽ የጣሰ እና ሥነ ሥርዓት የጎደለው የክስ አቀራረብ ነው፡፡

በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁን ጠቅሶ ያቀረበው ክስ የተመሠረተው ተከሣሾች "..የሽብር ቡድኑ መስራች "አባል ናቸው፣ የመሰረቱትም ቡድን".. ሽብርተኛ .." ነው ከሚል የተሣሣተ መደምደሚያ ተነስቶ መሆኑን የተከበረው ፍ/ቤት ተገንዝቦልን በተከሳሾች ላይ በሽብርተኝነት የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲደረግልን እናመለከታለን፡፡

2. በ2ኛ <u>ክስ ላይ</u> የቀረበ<u>ቡ መቃወሚያዎች፡-</u>

2.1 <u>ማሰብ የማያስከስስ እና የማያስቀጣ መሆኑን በተመለከተ፡-</u>

በወንጀል ሕግ አጠቃላይ መርህ ማሰብ (የወንጀል ተግባር ለመፈጸምም ቢሆን) አያስቀጣም፣ አስቀጥቶም አያውቅም፡፡ በኢትዮጲያ የወንጀል ሕግም የትኛውንም ወንጀል ለመፈፀም ማሰብ ያስቀጣል በሚል የተቀመጠ አንዳችም ድንጋጌ የለም፡፡ በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ በተከሣሾች ላይ ባቀረበው 2ኛ ክስ " ..ተከሣሾች ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በሁከትና በአመጽ ለመለወጥ በማሰባቸው በዋና ወንጀል አድራጊነት በፈጸሙት በሕገ መንግስት እና በሕገ መንግስታዊ ስርዓተ ላይ በሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሰዋል.." በማለት ያቀረበው ክስ ይህን መሠረታዊ የወንጀል ሕግ መርህ ያልተከለ እና የወንጀል ሕጉንም ግብ ያላገናዘበ በመሆኑ የተከበረው ፍ/ቤት ይህንኑ ግምት ውስጥ በማስገባት የቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ ተከሣሾችን እንዲያሰናብታቸው እናመለከታለን፡፡

2.2 <u>በሕቡዕ መደራጀት፣ የሥራ ክፍፍል መፍጠር እና የተለያዩ ሥልጠናዎችን መውሰድ ተብሎ የተገለፀውን በተመለከተ፡-</u>

ዐቃቤ ሕግ በዚህኛውም ክስ ተከሣሾች በሕቡዕ መደራጀታቸውን በመጥቀስ፣ የሥራ ክፍፍል መፍጠራቸውን እና የተለያዩ ሥልጠናዎችንም መውሰዳቸውን በመጥቀስ ክስ አቅርቧል፡፡ ሆኖም በሕቡዕ መደራጀትን አስመልክቶ በ1ኛው ክስ በተራ ቁጥር 1.3. ያቀረብናቸው መቃወሚያዎች በዚህ በ2ኛ ክስም ያቀረብናቸው መቃወሚያዎች ተደርገው እንዲመዘገቡልን እናመለከታለን፡፡

2.3 <u>ተከሣሾች የእመጽ ቡድኖችን አደራጅተዋል በሚል የተጠቀሰውን በተመለከተ፡-</u>

ዐቃቤ ሕግ ተከሣሾች የአመጽ ቡድኖችን አደራጅተዋል በማለት ባቀረበው ክስ የጠቀሰው አባባል ተከሳሾቹ አደራጅተዋቸው የተባሉትን ቡድኖች በግልጽ ለይቶ ያላስቀመጠ በመሆኑ የተከሣሾችን የመከላከል መብት የሚያጣብብና ግልጽነት የጎደለው ነው ተብሎ ከክሱ ውስጥ እንዲሰረዝ ትዕዛዝ እንዲሰጥልን እናመለክታለን።

3. <u>1ኛ እና 2ኛ ክሶችን በተመለከተ የቀረበ የጋራ መቃወሚያ ፡-</u>

3.1. <u>በአንድ ድርጊት ሁለት ክስ መቅረቡ አግባብ ስላለመሆኑ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 61/1)</u>

3.1.1. በሁለቱም ክሶች ተከሳሾች ፈፀሟቸው ተብለው የተዘረዘሩት ድርጊቶች አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ ስለመሆናቸው ከክሶቹ ይዘት በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ሆኖም በወንጀል ሕጉ ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት መሆኑ በተደነገገበት አንቀጽ 61 ንዑስ አንቀጽ 1 "... *ቢሕግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚደረጉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች የተደረጉት በአንድ የወንጀል ማድረግ ሐሳብ ወይም ቸልተኝነት ሲሆን እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈኑ ሲሆን፣ አድራጊው ተመሳሳይ ቢሆንም ባላቸው በሁለት ወይም ከሁለት በበለጠ ተደራራቢ ድንጋጌዎች አይቀጣም*." በሚል በግልጽ ተደንግጓል። በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት የሚለውን መርህ በሚቃረን ሁኔታ ተከሣሾች ፈፀሟቸው ባላቸው አንድ እና ተመሳሳይ ድርጊቶች ሁለት የተለያዩ የሕግ ድንጋጌዎችን ጠቅሶ ተደራራቢ ክሶችን ማቅረቡ የወንጀል ሕጉን መርህ እና የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌውን ያልተከተለ ነው በማለት የተከበረው ፍ/ቤት ክሶቹን ውድቅ እንዲያደርግል እናመለክታለን።

3.1.2.ከሳሽ ዐቃቤ ሕግ በአንድ በኩል በ1ኛ ክስ ላይ ተከሳሾች የተከሰሱበት ድርጊት ከመዘጋጀት ያላለፈ እንደሆነ አድርጎ እያቀረበ በሌላ በኩል ደግሞ ወንጀል ያላቸው ድርጊቶች ከሱ ከዝግጅት አልፎ በሙከራ ደረጃ የተፈጸመ አስመስሎ በ2ኛው ክስ ማቅረቡ፡-አንድን ድርጊት በሚቃረኑ ሁለት አቀራረቦች ሁለት ክስ በማቅረብ ከሕጉ መንፈስ ውጭ በተደራራቢ ክስ የተከሳሾችን መብት ለማጥበብ በሚመስል መልክ የቀረበ ክስ ስለመሆኑ በቀላ መረዳት ይቻላል። በመሆኑም የቀረቡትን ሁለቱንም ክሶች በተመሳሳይ የወንጀል ሕጉን መርህ እና የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌውን ያልተከተለ ነው በማለት የተከበረው ፍ/ቤት ክሶቹን ውድቅ እንዲያደርግል እናመለክታለን።

3.2 <u>የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) ሀ እና 32(1) ለ የትኞቹን ተከሣሾች የሚመለከት ስለመሆኑ ተለይቶ ያልተገለፀ ስለመሆኑ፡-</u>

ዐቃቤ ሕግ በሁለቱም ክሶች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32(1) ሀ እና ለ ጠቅሶ ክስ ሲያቀርብ፣ የትኞቹ ተከሳሾች በ32(1) ሀ ደረጃ እንደተሣተፉ የትኞቹ ደግሞ በ32(1)ለ ደረጃ እንደተሣተፉ ለይቶ አላስቀመጠም። ይህ በሆነበት ሁኔታ ተከሣሾች የተጠየቁበትን የኃላፊነት ደረጃ አውቀው ክሱን እንዳይከላከሉ የሚያደርግ በመሆኑ፣ ዐቃቤ ሕግ ከተከሣሾች ውስጥ ማን በ32(1) ሀ ደረጃ፣ማን ደግሞ በ32(1) ለ ደረጃ ተሳትፏል ለማለት እንደፈለገ ለይቶና ክሱን ግልጽ አድርጎ እንዲያቀርብ እንዲታዘዝልን እናመለክታለን።

3.3. <u>የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 38(1) በቀረቡት ክሶች ላይ መጠቀሱ አግባብ ስላለመሆኑ፡-</u>

ወንጀል ለማድረግ ማደምን በተመለከተ የተደነገገው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 38/1 ላይ የተገለፀው " ..ስለ ወንጀል ተካፋይነትና ቅጣትን ስለማከበድ የተፃፉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ.. " ነው።በመሆኑም ተከሣሾች በኅብረአበርነት ወንጀል ፈጽመዋል በሚል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32/1 'ሀ' እና 'ለ' ተጠቅሶ እያለ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 38/1 በተጨማሪነት የሚጠቀስበት ምክንያት የለም። በሌላም በኩል ድንጋጌው ክስ በሚቀርብበት ጊዜ በመክሰሻነት የሚጠቀስ ሳይሆን በቅጣት ጊዜ ተፈፃሚ መሆኑን የሚገልጽ በመሆኑ፣ ዐቃቤ ሕግ ያለቦታው ያስገባውና በክሱ ላይ የተጠቀሰው አንቀጽ 38/1 እንዲሁም በወንጀል ዝርዝሩ ውስጥ ስለአድማ ስምምነት ያሰፈረው አባባል በወንጀል ድርጊቱ ወንጀል የሚያደርገውን ድንጋጌ የማያሟላም እና የክስ አቀራረብ ሥርዓትን ያልተከተለ ነው በማለት ከክሱ እንዲወጣ የተከበረው ፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲሰጥልን እናመለክታለን።

3.4. <u>የቀረበውን የማስረጃ ዝርዝር በተመለከተ፡-</u>

3.4.1. ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው የማስረጃ ዝርዝር የምስክሮችን ብዛት፣ ስም እና የሚያስረዱትን ጭብጥ አልገለጸም። የምስክሮቹን ስም ላለመግለጽ የሰጠው ምክንያት በደፈናው " ...በሀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ እና በምስክሮች ጥበቃ አዋጅ መሰረት.." የሚል ነው። ሆኖም በተጠቀሱት አዋጆች ላይ የምስክሮችን ማንነት ላለመግለጽ በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጠው ".. የምስክሩ ሕይወት አደጋ ላይ መሆን .. ሆኖ እያለ <u>(የጸረ ሽብርተኝነት አዋጅ አንቀጽ 32)</u>፤ ይህ አደጋ ስለመኖሩ ሣያረጋግጥ በራሱ ጊዜ የምስክሮቹን ማንነት ከተከሣሾቹ መደበቁ

ከአዋጆቹ መንፈስና ዓላማ ውጪ ነው:: በተከሳሾች እምነት ምስክሮች ተብለው የተቆጠሩት ዐቃቤ ህግ በሰነድ ማስረጃነት ካቀረባቸውና ከተከሳሾች ላይ ተያዙ ተብለው በቀረቡት ሠነዶች ላይ ስማቸው ከሰፈረው ግለሰቦች ማንነት አይዘልም::

በመሆኑም የተከበረው ፍ/ቤት ዐቃቤ ሕግ የምስክሮቹን ማንነት ለመግለጽ የሚያስቸግር አሣማኝ ምክንያት ካለው እንዲያቀርብ ትዕዛዝ እንዲሰጥልንና ይህን ማድረግ ካልቻለ ግን በክሱ ላይ የምስክሮቹን ማንነት በግልጽ ዘርዝሮ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ እንዲሰጥልን እናመለክታለን::

የሆኖ ሆኖ ዐቃቤ ሕግ የምስክሮቹን ማንነት ሊገልጽ አይገባም የሚባልበት ምክንያት ቢኖር እንኳን የምስክሮቹ ብዛት፣ የትኛው ምስክር በየትኛው ተከሣሽ ላይ እንደሚመሰክር እና በምን ጭብጥ ላይ እንደሚመሰክር እንዲገለጽ ትዕዛዝ እንዲሰጥልን እናመለክታለን::

3.4.2. ዐቃቤ ሕግ ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ ዝርዝር በተራ ቁጥር ተለይቶ የተቀመጠ ሣይሆን በነቁጥ( bulet ) ተዘበራርቆ እና የትኛው የሰነዱ ማስረጃ ለየትኛው ክስ እና በየትኛው ተከሣሽ ላይ ምን እንደሚያስረዳ እንኳን የሚገልጽ አይደለም:: ከዚህም በተጨማሪ በማስረጃው መግለጫ ላይ የቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ርዕስ ናቸው ተብሎ በተገለፁት እና ከክሱ ጋር ተያይዘው በተሰጡን በርካታ ሰነዶች መካከል ፈጽሞ መጣጣም ስለሌለ እና በዝርዝር ውስጥ ተገልጾ ያልተያያዘ፣ ተያይዞ ደግሞ በዝርዝሩ ውስጥ ያልተገለፀ ሁሉ በመኖሩ ዐቃቤ ሕግ ማስረጃ አድርጎ የቆጠረው የትኛውን እንደሆነ እንኳን ለመለየት ተቸግረናል:: በመሆኑም ከሳሽ የሆነው ዐቃቤ ሕግ ክሴን ያስረዱልኛል የሚላቸውን ማስረጃዎች በወጉ ለይቶ ሕና ከላይ በገለጽነው መልክ አደራጅቶ ማቅረብ ሲገባው ፣የትኛው ማስረጃ ለየትኛው ክስ እና በየትኛው ተከሣሽ ላይ ምን እንደሚያስረዳ ባልተለየ ሁኔታ ማቅረቡ ተገቢ ካለመሆኑም በላይ እያንዳንዱም ተከሣሽ የቀረበበት ማስረጃ የትኛው እና ምን ያስረዳል ተብሎ እንደቀረበበት አውቆ ክሱን እንዲከላከል የማያስችለው በለመሆኑ፡ የተከበረው ፍ/ቤት ዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎቹን በአግባቡና በወጉ አደራጅቶ የማቅረብ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ትዕዛዝ እንዲሰጥልን እናመለክታለን::

የተከሣሽ ጠበቆች፡-

1. አምኃ መኮንን
Ameha Mekonnen
የማናቸውም ፍ/ቤት ጠበቃና አማካሪ
Consultant & Attorney at Law

2. ሽብሩ በለጠ